# አዘጋጅ   አባተ ደጋነ

<u>ሰኔ ቀን 8 2012 ዓም</u>

## *ብዙ ቻር መሆን ያስጠቃል!*

## *ታሪክ አልባ አገር*

ከአሥር ቀን በፊት ነው አንድ ምሁር ስለሱዳን አንስተው የሱዳን መንግሥት ጠንካራ ጎን እንዳለው ሲናገሩ ሰማሁኝ። የምሁሩ አቀራረብ በጥናት ላይ የተሞረኮዘ ቢሆንም የሱዳን ታሪክ ወይም ሱዳን ተብላ የሚትጠርው አገር ሕሊውና ያገኘችው ከጀነዋሪ(ጥር) 1956ዓም ነው፡ በመሠረቱ እኔ የሠራዊት አባል የነበርኩ እንጂ ተመራማሪ ወይም ምሁር አይደለሁም፣ ጽሑፊም ለትችት የታሰብ እንዳልሆነ አንባቢ እንዲረዳልኝ እጠይቃለሁ።

ሱዳን አገር ተብላ ሕሊውና ያገኘችው ከላይ እንደጠቀስኩት ከ1956 ዓም እንደሆነ ታሪኳ ይመሰክራል፥{ *ቢላድ አል ሱድ*} የሚለው ቃል የመጣው ከአረቦች ሲሆን ትርጉሙ የጥቁር ምድር ማለት ነው፡ ጊዜው እየረዘመ ሲሄድ እኔ ጥቁር ነኝ ለማለት ተፈልጎ *ሱድ አን ትርጓሜው {እኔ ጥቁር ነኝ}* የሚል ነው፥ እንግዲህ ሱዳን የሚለው ስያሜ የዓረቦች በጎ ችሮታ እንጂ ራሳቸው ሱዳኖች የሰየሙት እንዳልሆነ ታሪክ ይመሰክራል። ሱዳኖች እስከ ቅርብ ጊዜ  ድረስ ዝም ብለው የሚኖሩ እንጂ የነፃነት ትርጉም የማያውቁ፥ ዓለም ምን እንደምትመስል ሣይረዱና ሣይገነዘቡ የኖሩ ሕዝብ ናቸው ለማለት ይቻላል፥ ሱዳን ለመጀምሪያ ጊዜ አንግሎ ኢጂፕሺያን ተብላ የተጠራችው በ1889 ዓም ነበር፣ እንግሊዝና ግብፅ ስምንት ክፍለ አገራት የነበራትን ግዛት ሱዳን ብለው የጠሩዋት ከሌሎች ከመካከለኛ እስከ ምዕራብ አፍሪካ ከሚዘረጋ ቀጠና ለማለት እንደነበር የዛሬ አዛውንት ሱዳኖች ይናገራሉ

፥በወቅቱ ሱዳን የሚለው ቃል ዛሬ ከሳሃራ ደቡብ ሣህል አገሮች ተብለው የሚጠሩ ቀጠና የሚያጠቃልል ነበር። ብዙ የአፍሪካ አገሮች ለነፃነታቸው ሲታገሉ ሱዳኖች ከእንቅልፋቸው እንዳልነቁ ይነግገራል፥ ሱዳኖች በመሃዲ አመራር ሰጪነት ተዋግተው የነበሩ ሃይማኖትን ለማስፋፋት ሲሆን ዓላማቸው

ከኢትዮጵያ የክርስትናን ሃይማኖት ለማጥፋት እንደነበር ብዙዎች የሚያነሱት ነው።

-ሱዳን ሕዝቦቿን ወይም መሬቷን የሚገልጽ ታሪክ የሌላት የአፍሪካ መሬት ስለሆነች የድንበርም ሆነ የክልል ጥያቄ ሊኖራት የማይገባት ቀጠና ናት፥ ሱዳን የመሬት ጥያቄ የሚታነሳው ከኢትዮጵያ ብቻ ነው። ሱዳን ይህን ጥያቄ የምታቀርበው በራሷ ተነሣሽነት ሣይሆን ከአረብ አገሮች ግፍት በተለይ ከግብፅ ነው፥ ግብፆች በጥንት ዘመን ኢትዮጵያን የእግዚአብሔር ቤት ብለው ይጠሯት እንደነበር ይነገራል፥

አንግሎ ኢጅፕሺያን ሱዳን በ1956 ዓም ነፃነቷን ብትታደልም እስከ ዛሬ ድረስ ከግብፅ የእጅ አዙር አስተዳድር ነፃ ያልወጣች አገር ስትሆን ሤረኛ አመራር የሚፈልቁባት እኩይ ግብር የሚጠነሰስባት ክልል ናት። ግብፅ ሱዳንን እንደፈለገች ታሾራታለች፥ ለዚህ ማስረጃ ቢያስፈግ የአስዋን ግድብ ተገምብቶ እንደተጠናቀቀ ዝርያቸው ከኢትዮጵያ ተብለው የሚታሙት ሐልፋውያን ለኢትዮጵያ መረጃ ሊያስተላልፉ ይችላሉ ብለው ግብፆች ስለተጠራጠሩ ቦታውን ለቅቀው እንዲሄዱ ግብፅ ለሱዳን ትዕዛዝ ስለሰጠች ሐልፋውያን ከኖሩበት ቄያቸው ተፈናቅለው ከሬሎቹ ወደ ምሥራቅ ተከዘ አጠገብ ሠፈሩ ይህ ቦታ ዛሬ ፤ሐልፋ ጀዲዳ(አዲሱ ሐልፋ) ተብሎ ይጠራል፤፣ ሐልፋ አንኄድም በየቦታው ተብትነው ይኖራሉ፥ ሌላ ምሣሌ ካስፈለገ በ2000 ዓም ግብፅ ሐለብ የሚባል የሱዳንን መሬት ወሪራ ያዘችው። ነፍስ ካለ መንቀሳቀስ አይቀርም ይባላልና የሱዳን መንግሥት የሐለብን አውራጃ ወደ ሱዳን ለመመለስ ሲያቧተር የግብፅ ፐረዝዳንት ሆስኒ ሙባረክ <u>፤ሐለብ ታሪክ እንደሚነግረን የኢትዮጵያ ግዛት ነበር፥ ሱዳን የሚባል አገር ከታሪክ መዝገብ ላይ የለም፥ መሬቱ የኢትዮጵያ ነው ፣ኢትዮጵያ መሬተን ስጡኝ ብላ ከጠይቀችን እንሰጣታለን፥</u> ብሎ በመናገሩ ሱዳን መለእከተኛ ወደ ሙባረክ ልካ የሐለብን አውርጃ ለግብፅ መርቃ ከመስጠትም አልፋ ዱንጉላ ከተባለ ግዛቷ መሬት ቆርሳ በመስጠትዋ በሱድን ውስጥ የፓን አፍሪካ ንቅናቄ አባል ዶር መሐመድ ጃላል የሱዳንን መንግሥት ከስሶ መሬቱ ለሱዳን ቢያመለስም ፓን አፍሪካውያን አባሎቹ ከፍተኛ እንግሊትና ስቃይ ደርሶባቸዋል።

# ክፍል ሁለት

## ያለ አቅሟ የጠበደለች አገር፣

የመሬት ቁንጣን ያሰከራት ሱዳን የብዙ አገር ጎሳዎች መኖሪያ ናት፥ ከሩቅ ምሥራቅ፣ከላቲን አሜሪከ፣ ከምሥራቅ ኤውሮፓ፣ከመካከለኛ ምሥራቅ፣ ወዘተ ይኖሩባታል፥ ብዙዎች የውጭ አገር ሰዎች የሚኖሩት በየትላልቅ ከተሞች ሲሆን በየገጠር የሚኖሩ አፍሪካውያን ናቸው፥ በተለይ በምሥራቅ ሱዳን የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ናይጀሪያ(ፋላታ)ናቸው፥ እነዚህን ሁሉ ጨምሮ የሱዳን ሕዝብ ብዛት 43›824›769 ሲሆን የመሬቷ የቆዳ ስፋት 1.886.068 እስኩዌር ኪሜትር ነው፥ ይህም ከዓለም አገሮች ስወዳደር ጀርመንን 5 ጊዜ ትበልጣለች፣ እንዲሁም ከሰሜን አሜሪካ ስትተያይ የአሜሪካ አንድ አምስተኛ ለመሆን ጥቂት ይቀራታል፥ ከጂቡቲ ጋር ስትወዳደር 81 ጊዜ ትበልጣታለች።

ሱዳን ምኞቷ እውን ቢሆንላት ኢትዮጵያን ሠራዊት ደምስሳ መሬቷን ብትወስድ የቀን ሕልሟ የሚሳካ ይመስላታል፥ ሱዳንን የሚያቃዣትና እንቅልፍ የሚያሳጣት ትልቁ ከነበረችበት ጨለማ ወደ ብርሃን ስትወጣ ትልቁ ሕልሟ የሰፊ ለም መሬት ባለበት መባል ነው።

ሱዳን ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለማጥፋት የማትፈነቅለው ድንጋይ፣ የማትሸርበው ሤራ የለም፤ የሱዳን መሬት በአብዛኛው የሚጠቀሙበት የዉጭ ባለሐብቶች ናቸው፣ ሱዳን ዜጎች በአብዛኛው ዓረብ አገር ተሰድደው ይኖራሉ። በተለይ ከምዕራብ አፍሪካ ለፀሎት ሣዑዲት አረቢያ ደርሰው የሚመለሱ ወደ መጡበት ከመመለስ ሱዳን አገር ይቀራሉ።የሱዳን መንግሥትም ወደ ምሥራቅ ገዳሪፍና ከሰላ ይወስዷቸውና ዜግነት ይሰጧቸዋል። ዋናው እቅዳቸው የኢትዮጵያን መሬት ለማስያዝ ነው፣ በ2010 ዓም የሱዳን መንግሥት ለ17000 የፍልስጤም ስደተኞችን በአገሩ ለማስፈር ለተ.መ.ድ ጥያቄ አቅርቦ ነበር፣ ዋና እቅዱዋ ሱዳን

ለፍልስጤማውያን አዝና ሣይሆን ሕዝበ ጽፍ(Demography)ለመቀየር ነበር። ሆኖም ግን ተመድ ሤራውን ተረድቶ አልፈቀደም።

## <u>ክፍል ሦስ</u>ት

## <u>በሁለት ሰዓት የ30 ኪሎ ሜትር ሽሽት</u>

በሱዳን አገር በስደት ረጅም ዓመታት ስለኖርኩኝ አንዳንድ ቦታዎችንም እየተዘዋወርኩኝና አንዳንድ በእድሜ የገፉትን ሱዳኖች ስለሱዳን ታሪክ የጠየኳቸው የሰጡኝን ከግንዛቤ በማስገባት እውነትም ሱዳን የምትባል አገር እንደለለች ለማወቅ ቻልኩኝ፣ የሱዳን የቦታዎች ሲያሜ ስመለከተው ከኢትዮጵያ ጋር የተያያዘ ሆኖ አግኝቻቸዋለሁ፣ አንዳንድ ስለታሪክ ያውቃሉ ብለው ሰዎ የጠቆሙኝን እንደዋዛ አድርጌ አነጋግረአቸዋለሁ። ከአነጋገርኋቸው መካከል አደም መሐመድ ኡመር የሚባሉ የ92 ዓመት አዛውንት ነዋሪነታቸው ገዳረፍ የሆኑ  ስለኢትዮጵያና ስለሱዳን ጠይቄአቸው ሲያጫውቱኝ ከምስር አጠገብ ከነበረው ወረዳ ብንጀምር አሉና« ሐልፋውያን በአባታቸው ሐበሻ ናቸው፣ሞግረን ( ጥቁር አባይና ነጭ የሚገናኙበት ወይም ምድማር) ዛሬ የካርቱም እምብርት ተብላ የምትጠራ የኢትዮጵያዊ ንጉስ አፄ እያሱ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ነበር፣ ሦባ ንግሥት ሳባ ወደ እሥራኤል አገር ስትሄድ ያረፈችበት ሲሆን ቦታው በኢትዮጵያ መንግሥት በርስትነት ተይዞ ሣለ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሰፈረውበት እንደነበሩ ሲነገር አማን አንዶም የተባሉ የኢትዮጵያ የጦር መኮንን የተወሰኑ ሰዎችን  አስከትለው ሦባ እንደቆዩ አዛውንቱ አደም ነግረዉኛል፣ በመቀጠልም መድሐኔ ወይም መድኔ እንዲሁም ዝናር የሐበሻ አገር እንደነበሩ ከፊል ሕዝቡ አሶሳ በሚባል የኢትዮጵያ መሬት ይኖራል፣የዝናር የጥንት ስሟ መተማ ሆኖ የሐበሻ የመሬት ላይ ወደብ እንደነበረች አጫውቶኛል፥ አደም የነገሩኝ ምን ያህል እዉነት ነው በማለት መጽሐፍ ሣፈላልግ <u>SHORT HITORY OF THE SUDAN</u> የሚል በመሃዲ ማንዶሪ የተፃፈ መጽሐፍ አገኘሁ፣ ጊዜ ውስጄ አነበብኩት፥ አደም ካጫወተኝ የሰፋ እውነት አገኘሁ፥ አደም በተጨማሪ አፄ ምኒልክ ለኢንግሊዝ መንግሥት በድብዳቤ የግዛታቸውን ስፋት እስከ ሰሜን

አትበራ ከተማ መሆኑን በማህተም የተደገፈ ሰነድ ሰጠኝ፣ ሰነዱም ዛሬ በእጄ ላይ ይገኛል፥ ከዚህም ሌላደማዚንና ስንጃ አብደላ የሚባሉ አውራጃዎች ጣሪቅ ከሚባል ጓደኛቸው ጋር ሆነው የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበሩ አረጋግጠውልኛል፥ በመቀጠልም ስለገዳሪፍና ስለምሥራቅ ሱዳን ጠይቄአቸው መሬቱ የኢትዮጵያ መሆኑን እንኳንስ ሱዳናውያን ቀርተው ትላንት ከናይጀርያ ወደ ሱዳን መጥተው የሰፈሩ ፋላታዎች ያውቁታል። ለነገሩ ያህል እንጂ ኢትዮጵያ በገዳሪፍ ወይም በደማዚን ቀጠና ጦርነት ብትከፍት የሱዳን ጦር ውሻ እንዳባረረው ሕፃን ጥሎ ከመሸሽ ሌላ የተከስ መልስ ይሰጣል ብሎ ማመን አስቸጋሪ ነው፥ ምክንያቱም በያንዳንዱ ወታደር አእምሮ ውስጥ፡ሰርጾ ያለው« *ለምን በሰው መሬት ላይ እንሞታልን» የሚል ሲሆን ወላጆችም ቢሆኑ ልጆቻቸው በከንቱ እንዲሞቱባቸው ስለማይፈልጉ ነገሩ አስቸጋሪ ነው»* በማለት አጫውተውኝ ነበር። ሩቅ ሣንሄድ በታሕሣሥ ወር 1994 ዓም የኢትዮጵያና የሱዳን ጦር በምሥራቅ ሱዳን ውጊያ ገጥመው የኢትዮጵያ ጦር በሁልት ሰዓት ውጊያ የሱዳንን ጦር ከ30 ኪ ሜትር በላይ ወደ ውስጥ እንዳባረረው በዓይኔ አይቻለሁ፥ ለምን እንደሸሹ ወታደሮቹ ሲጠየቁ«ለሰው መሬት ብለን ለምን እንሞታለን»የሚል መልስ ሲሰጡ ተሰምቷል። የዕለቱ ጦርነት ዉጊያ ሣይሆን የማራቶን እሽቅድምድም ነው ቢባል አያስገርምም ብለው የሚተቹ ተመልካቾችም አጋጥሞኛል። በዕለቱ የሸሸ የሱዳን ወታደሮች ብቻ ሣይሆኑ ተቋሞችም ያለውን ንብረታቸውን ጭነው ወደ ካርቱም ሸሹ።

ዉርደቱን የተረዳ የበሽር መንግሥት ም| ፕረዝዳንት ጀኔራል ዙበርን ወደ አዲስ አባባ ልኮ ከመለስ ጋር ተገናኝቶ አቤቱታ ሲያቀርብ «ከፈለጋችሁ ተስማምተን መሬታችን ነው የምትሉትን እንመልስላችሁ፥ ሌላም ከፈለጋችሁ ውጊያው ይቁምና እንነጋገር፥ ተቃዋሚዎችን ከፈለጋችሁ ልናስረክባችሁ እንችላለን» ብሎ ሐሳብ ሲያቀርብ መለስ ከመሬት ይልቅ ተቃዋሚዎችን እንዲያስረክቡት ስለተስማማ ዙበር አዲስ አባባ ሆኖ በስልክ የመለስ ተቃዋሚዎች እንዲታሠሩ ስለወሰነ በሱዳን የሚንቀሳቀሱ የተቋሚ አመራሮች ተይዘው እንድታሠሩ ከሱዳን መንግሥት መመሪያ ተላልፎ ብዙዎች ሲታሰሩ ፣ የተባበሩት መንግሥታት ጣልቃ ስለገቡ በጅምላ ማስረከቡ ቀርቶ በተናጠል እያፈኑ ማስረከብ ወይም በሥውር ማስገደል ጀመሩ። ያን ጊዜ በተደረገው ውል መሠረት በሺህ የሚቆጠሩ የፖልቲካ ስደተኞች የኢትዮጵያ ፀጥታ ተላልፈው ተሰጥተው ሲገደሉ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የዳፎር

ተቃዋሚዎች ከኢትዮጵያ ለሱዳን መንግሥት ተላልፈው ተሰጥተው በግፍ ተጨፍጭፈዋል፥ ይህ ግፍ እንዲፈጸም ውል የተፈራረም  የሱዳን መንግሥት ምክትል ፕሬዝዳንት ዙበር ብዙም ሣይቆይ በአደጋ ሞተ። በዙበር በተፈፀመ ግፍ በአዲስ አባባ ማእከላዊ እሥር ቤት በርካታ ንፁን ዜጎች አልቀዋል። በማእከላዊ እሥር ቤት ከሞቱት መካከል ጀግናው አጣናው ዋሴ አንዱ ነበሩ።

## ክፍል አራት

## ባቢከር አደም (ፉላታው)

በመሠረቱ በሱዳን ውስጥ የሚኖሩ ጎሳዎች ከ597 ይበልጣሉ፣ ከነዚህ ጎሳዎች መካከል ባሶንዳ ከሚባል አከባቢ የሚኖር አንድ ስሙ ባቢከር አደም የሚባል ፈላታ ነብር ወደ ገዳሪፍ የሚሄድ መጓጓዣ እይጠብቅን ጫወታ ጀመርን መኪናው ጊዜ ስለወሰደ ከኢኮኖሚ ጫወታ ወደ ፖለቲካ ጫወታ ተሸጋገርን « ለመሆኑ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ጦርነት ቢነሣ ምን ትሆናላችሁ» ብዬ ብጠይቀው«ሁለት እድሎች አሉን፣ አንደኛው የኢትዮጵያ ሠራዊት አዋቂ ነው የማይተኩስበትን ሰው አይነካም፣ ይህንን ለማለት የቻልኩት ከአለፈው ልምድ በመነሳት ነው፣ ሁለተኛው የኢትዮጵያ መንግሥት ውጡ ከአገራችን መሬት ከአለን ወደ ናይጀሪያ መመለስ ነው፣ ይህን ዓይነት ጭካኔ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደማያደርግም እርግጠኛ ነኝ፥ የሱዳን መንግሥት ዉጡልኝ ካለ ግን እንሟገታለን እንጂ አንወጣም፣ ምክንያቱም መሬቱ የኢትዮጵያ እንጂ የሱዳን አይደለምና»። የባቢከር አነጋገር በጣም ገረመኝ፥ ባቢከር ከናይጀርያ የመጣ ቅጠል በጣሽ የኢትዮጵያንና የሱዳንን መሬት ለይቶ ሲያዉቅ የኛ መሪዎች«ከሱዳን መንግሥት ጋር ድንበር ልንካለል ብለን እነርሱ የእንግሊዙ ሻልቃ ጉዌን በከለለው

መሠረት ካልሆነ እያሉ አስቸገሩን. ሲሉ..........ይነግሩናል። ለመሆኑ ሻለቃ ጉዌን ድንበር የመከለል ሥልጣን ነበረው ወይ? መልሱ አልነበረውም አላደረግምም፥ የማድረግ ሥልጣንም የለውም ነው ምላሹ፥ የዛሬ መሪዎቻችን የሻለቃ ጉዌን ድንበር መከለል አሜን ብለው ከተቀበሉ ሱዳንና ግብፅ በ1929 ዓም ስለተዋዋሉት

ስለዓባይ የተፈራረሙትን ሰነድ ለምን አንቀበልም አሉ?? እኔ ይህን ቃል ስሰነዝር ስለዓባይ ጉዳይ ሣቆረቁረኝ ቀርቶ ሣይሆን ቅጠል በጣሹ ፈላታ የሚመሰክረውን መሪዎቻችን ለምን አያዳምጡም?? ጠረፍ የሚኖር የኢትዮጵያ አርሶ አደር የቅድመ አያቱን ርስት አሳልፎ ላለመስጠት የመጨረሻ ትንቅንቅ እያደእረገ ይገኛል። በተለይ የአማራ አርሶ አደር እየተደፈረ ነው፥ የአማራ ገበሬ አርሶ ሰብሉን ሊሰበስብ ሲዘጋጅ የሱዳን ወታደሮች እሳት ለቅቀውብት ያጋያሉ፣ አራሹም ድንገት በእጃቸው ከገብ የመትረፍ እድሉ አጠራጣሪ ነው፣ የሱዳን ወታደሮች በሻለቃና በብርጌድ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መሬት እየገቡ ከብቶችን ሲዘርፉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በዝምታ ይመለከታል፥ በሌላው አንጻር ሕዝቡ ራሱን እንዳይከላከል የኢትዮጵያ መንግሥት ትጥቁን እየቀማው ነው፥ ራሱን እየተከላከለ አገርን የሚጠብቀውን አርሶ አደርን ሽፍታ ብለው የሚዋጉ አካላት አሉ፥ ይህንን ጉድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከያለበት ሆኖ መስማት ይኖርበታል። መስማትም ብቻ ሣይሆን መሬታችንን ለመከላከል በሚዋደቀው አካል ጎን ተሰልፎ የአባት አደራውን እንዲወጣ ወገናዊ ጥሪዬን አቀርባለሁ። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በየትኛውም ዓለም የሚኖር በሕዳሰ ግድብ ዙሪያ እንደተሰባሰበ ሁሉ በሱዳን ክልል ወሰናችን ገዳሪፍ መሆኑን ድምፁን እንዲያሰማ እና ጠቅላይ ሚኒስትር አብይም ሆነ ምክር ቤቱ ታሪካዊ ስሕተት እንዳይፈጽም በጠረፍ ላይ ለሚዋደቀው ጀግና ቁሳዊና ሞራላዊ ድጋፍ ይሰጠው ዘንድ በርካታ ኢትዮጵያውያን ያሳስባሉ።

## *ክፍል አምስት*

## *ሣይዋጉ ስለጦር ስልት ወሬ ወይስ የእብለት ፉከራ፣*

ነገሩ ስለ አፄ ዮሐንስ አሟሟት ለመተረክ ይመስላል፥ የሱዳን ፕሬዝዳንት አልበሽር ሠራዊታቸው በሁለት ሰዓት ከ30 ኪ ሜትር በላይ ከሸሸ ከወር በኋላ ከሣኡድ አረብያ ከጉብኝት መጥተው በተለብሸዥን መስኮት ብቅ ብለው ሲፎልሉ ወይም ሲፎክሩ«*እኛ የጦር ስልት አሳምረን እንውቃለን ፣ከፈለግን አንገት እንቆርጣለን>» ማለታቸው ብዙ ሰዎችን አስቋል።*

ስለእውነት ለመነጋገር ከተፈለገ በአፄ ዮሐንስ የሚመራ የኢትዮጵያ አርሶ አደርና አርብቶ አደር ሠራዊት ደርቡሾችን ከሁለት መቶ ኪ ሜትር በላይ አባርሮ ውጊያው ሊያበቃ ገደማ አፄ ዮሐንስ እንደቆሰሉና ከዚያም ወደ ድንኳናቸው ተወስደው ጥቂት ከታከሙ በኋላ ራስ አሉላን አስጠርተው ተናዝዘዋል፥ ለራስ አሉላም ወራሻቸውም መንገሻ አደራ እንደሰጡ ብዙ የታሪክ ፀሐፊዎች መዝግበዋል፥ በውጊያ ላይ ንጉሡ ይሰው እንጂ ድሉ የኢትዮጵያውያን ነበር፣ የማይካድ ሐቅ መሆኑን ብዙ ሱዳኖች ያረጋግጣሉ፣ ስለዚህ ሐቅ ያውቃሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ሣነጋግራቸው በእርግጠኝነት ደፍሮ ሰሱዳን ጥንታዊነት የሚከራከር አላግጠመኝም፣ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ያነጋገርኹአቸው ግን በንዴት« አነጋገር የጎጃምን ሕዝብ ስለፈጁ አንገታቸው መቆረጡ ሲያንስ ነው» ሲሉ አንዳንዶች ደግሞ«ንጉሡ ቢሳሳቱም አንገታቸውን የተሰየፉት በኢትዮጵያ ክብር ስለሆነ መወገዝ የለባቸውም» እዚህ ላይ የራሱን ግምጋሜ ሊሰጥ የሚገባው ባለሙብት አንባቢና ይመለከተኛ የሚል ካልሆነ ግላዊ ሐሳቤን ከመስጠት እቆጠባለሁ።

ስለአፄ ዮሐንስ አንገት በደርቡሾች መቆረጥ የተምታቱ ሐሣቦች በአዕምሮዬ ውስጥ እየተመላለሱ ስለሆነ በግል ከማሰብ ሰዎችን ማነጋገር እንዳለብኝ ባምንም ጥያቄዬ በስደት ጎኔ ላይ ክትትል ቢያስከትልብኝም ሐቁን ማወቅና መልሶ ማሳወቅ አገራዊ ግዴታ እንዳ አለብኝ ራሴን አሳምኜ ቀጠልኩበት።

በዚህ ታሪክ ዙሪያ ከልጅነቴ ጀምሮ በአእምሮዬ ውስጥ .ይጉላላ የነበረ «ደርቨሾች በመተማ ላይ የአፄ ዮሃንስን ራስ ቆርጠው ካይሮ ከተማ ውስጥ በግመል ላይ አንጥልጥለው አዞሩ .........» በሚለው የታሪክ ጽሑፍ መንፈሴ ይረበሽ ነበር። ስደቴ ከፍቶ ሱዳን ከገባሁ ጀምሮ ይህን ነገር ለማወቅ መጣር እንባለብኝ አመንኩኝ፥ ለጥያቄዬ ምላሽ ለማግኘት በእድሜ ከገፉ ኢትዮጵያውያን ጀመርኩኝ፥ ለጊዜው አጥጋቢ ምላሽ ስለአላገኘሁ ስለጦርነቱ አንዳንድ ሱዳኖችንም መጠየቅ ጀመርኩኝ።

እንደ አጋጣሚ የደቡብ ሱዳን ተወላጅ ከሆነ ብ› ጄኔራል ቨክቶር ጋር ተዋወቅሁ፥ ብ.ቨክቶር እድሜው ገፋ ያለ በሱዳን ፖሊቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ሰው ነው፣ ከወጣት እድሜው ጀምሮ የፖለቲካ ተሳትፎው ከፍተኛ መሆኑን ከአቀራረቡ መረዳት ይቻላል፥ብዙ በመቀራረባችን ስለዓለም የፖሊቲካ ጉዳይ እያነሳን ስንወያይ ስለድርቨሽ አነሳንና እንደሚከተለው አጫወተኝ።

*« ይህ ዓይነት ጥይቄ ሲቀርብልኝ የመጀመሪያ ጊዜ ነው፣ ኢትዮጵያውያን ስለራሳቸው ቀርቶ ስለዓለም ብዙ ቁምነገሮችን ያውቃሉ ብዬ ነው የማስበው፣ ስለንጉሥ ዮሐንስ ሣልገልጸህ ስለወቅታዊ እና ስለነባራዊ ሁኔታ ካንተ ልሰማ እወዳለሁ፡ ዛሬ መጋቢት ወር 1995 ዓም ነው፥ ለመሆኑ የዛሬ ሦስት ወር ገደማ በሱዳን ምን እንደተፈጸመ ሣታውቀው አትቀርም ፣ የኢትዮጵያ ጦር በሱዳን ጦር ላይ ወረራ ሲከፍት የሱድን ጦር ምን ያህል ወደ ኋላ አፈገፈገ ወይስ ሸሸ??መልሱን ላንተ ትቻለሁ፥ ወደ ንጉሥ (አፄ ዮሐንስ)ራስ መቆረጥና አል ቃይራ(ካይሮ ማለቱ ነው)መንገላታት ከሱዳን አመራር አካል ዉጭ ሌሎች ሱዳኖች አያምኑትም፥ ሌላ ጥያቄ ልጨምርህ የሚሸሽ ጦር እንኳንስ ራስ መቁረጥ የራሱን ጓድ ማዳን ይችላል ወይ?? በዉጊያ ላይ ትንሽ መዋሸት ይቻላል፣ግን! ግን! ንጉሥን ያዉም ኢትዮጵያዊን!! ለጥያቄህ መልስ ባልሰጥህም የምጠቁምህ አንድ ነገር አለ ይኼውም ትላልቅ ኢትዮጵያውያንን ጠይቃቸውና መልሱን ይሰጡሃልና ፥ካልሰጡህ ሌላ ጊዜ እንውያያለን » ብሎኝ ተለያየን።*

ጄኔራሉ የነገረኝ ቁምነገር ከባድ ብሎ ታየኝ፣ ወታደር ስለነበርኩ ከአቀራረቡ የኔንም አክዬበት ብዙ ለማሰላሰል ቻልኩኝ፥ እውነትም የሚሸሽ ጦር ማረከ ፣ ገደለ፣ አንገት ቆረጠ ወዘተ ብሎ ማውራት አጉል ትሪክትና አሳፋሪ ነገር ስለሆነ

ሃቁን ለማወቅ ሌላ ምንጭ መፈለግ ቀጠልኩኝ። ወደ ቀጣዩ ስንኙ ከማለፌ በፊት ጄ. ቭከቶር ከጠቆመኝ አንዱ *የሚሸሽ ጦር አይማርክም* ያለው ነው። በሁለት ሸሸት ወቅት የሱዳን ወታደሮች የጉልበት ሥራ ተቀጣሪዎችን ይዘዋቸው ጠመንጃ አሸከሚቸው *የተናረኩ የኢትዮጵያ ጦ*ር ብለው በተሌቭዥን መስኮት እንዳቀርቧቸው ማንም ኢትዮጵያዊ ያየውና የሚመሰከረው ነው፡

## *ክፍል ሰድስት*

## በእንጥልጥል ላይ ያለ ጥያቄ

*አፄ ዮሃንስ እንደት ተሰው የሚለው ጥያቄዬ በሌሎችም ኢትዮጵያውያን አእምሮ ይጉላላ ይሆን ወይስ ተረስቷል የሚለው የብዙ ኢትዮጵያውያን ጥያቄ ነው የሚል ግምት አለኝ፣ የዚህ ጽሑፍ አስፈላጊነት የሱዳን ዘመን ያልለወጠ ለወደፊትም* የማይለወጥ ሤራ ኢትዮጵያዊው ትዉልድ እንዲያውቅ በሚል እንጂ እኔ የዘር ሐረግ ወይም ስለአለኝ አይደልም። እዚህ ላይ የዚህ መልዕክት አንባቢ እንዲረዳልኝ የምጠይቀው ማንኛውም መሪ ደካማ ጎን እንዳለው ሁሉ እርሳቸውም ደካማ ጎን የላቸውም ለማለት አይደለም፣ በተለይ በጎጃም ሕዝብ ላይ ግፍ ፈጽመዋል ተብለው በሰፊው የሚነገረውን ለማስተባበልም አይደለም። መሪዎቻችን ሕዝብን ሲበድሉ ይቅርታ መጠየቅ በአገራችን ስላልተልመደ እንጂ የተከበረ የጎጃም ሕዝብ ይቅርታ ቢጠየቅ ይቅር ለእግዚአብሄር እንደሚል ማንም የሚስተው አይመስለኝም፣ አሁንም ቢሆን ጊዜው አልፏል፣ አብቅቷል ለማለት ሳይሆን አባት ስለበድለ ልጅ ይቅርታ ቢጠይቅ ስለማያስነውር አፄ ዮሃንስ ለበደሉት የጎጃም ሕዝብ ክቡር ልዑል ራስ መንገሻ ይቅርታ ቢጠይቁ ቅሬታው ሊፋቅ ይችላል የሚል የግሌ ግምት አድሮብኛል። ለዚህ ሐሣቤ መንደርደሪያ የሆነኝ ፕረዝዳንት እሰይያስ ወደ አማራ ክልል ዘልቀው ይቅርታ ሲጠይቁ የአማራ ሕዝብ በክብር ይቅር ብሎ እንደተቀብላቸው በዓናችን አይተናል። ስለሆነም ድፍረት አይሁንብኝ እንጂ ክቡር

ልዑል ራስ መንገሻ በሕይወት እያሉ የጎጃምን ሕዝብ ይቅርታ ብጠይቁ ይህ በየጊዜው የሚነሳው ዉግዘት ይወገዳል ብዬ እገምታለሁ።

ወደ ዋናው ርዕሴ ልመለስና አፄ ዮሃንስ የቆሰሉት የዛሬዋ መተማ ሣይሆን አምራኩባ ከሚባል ቦታ እንደሆነ ሱዳኖች ያረጋግጣሉ። አፄ ሚኒልክ ከኢንግሊዝ ተወካይ ጋር አንድ ጊዜ ሲነጋገሩ  _ገዳሪፍን አትንኩብኝ ንጉሤ የወድቁበት ነዉና !!_ ያሉትን በርካታ ሰዎች እንደሚናገሩት የደርቭሽ ጦር የአፄ ዮሃንስን አንገት ቆርጦ እንዳልወሰደም ይታመናል፥

ሱዳንች በኢትዮጵያ አዲስ መንግሥት በመሠረተ ቁጥር _የንጉሡን ራስ ውሰዱ_ እያሉ ቢወተውቱም ያዳመጣቸው የኢትዮጵያ መሪ የለም፣ መሪዎቻችን በይፋ ባይናገሩም ለሱዳኖች _የተቆረጠ ራስ የአፄ ዮሃንስ ለመሆኑ ማስረጃ አቅርቡ እንደሚሉ አንድ ሰምን_ ሹክ ተብያለሁ።

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የሚሉት አፄ ዮሃንስ አምራኩባ ላይ መሰዋታቸው ያምኑና አስከረናቸው ወደ ትግራይ እንደተውሰደ ይናገርሉ። በጣም ውስጥ አዋቂዎች ናቸው የሚባሉ ደግሞ አስከረናቸው ደብረ ዳሞ እንዳረፈ ይጠቁማሉ፣ ማረጋገጫውስ ተብለው ሲጠየቁ በሚስጥር መልክ ወደ ክቡር ልዑል ራስ መንገሻ ያመለክታሉ። ሰው ቋሚ አይደለም ታሪክ ግን ሕያው ነው፣ እኚህ ንጉሥ የወደቁት ኢትዮጵያን ከወራሪዎች ለመታደግ ሲሉ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው፣ ስለሆነም ታሪካቸው ተድበስብሶ መቅረቱ ተገቢ ካለመሆኑም ባሻገር የውሽት ትርክት አንግበው ለተሱት ልብ አልባ ሱዳንችን አፍ ማስያዣ ይሆናል ብየ እገምታለሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሱዳኖችን የሚያስደነብራቸው ክቡር ልዑል ራስ መንገሻ የሑመራን መንገድ ያሠሩት የአፄ ዮሃንስን ደም ለመበቀል ነው ይላሉ።የሱዳን መንግሥት ልዑልን ይፈሯቸዋል። ለፍርሃታቸው ሁለት ስበብ ይጠቅሳሉ፣አንደኛው ልዑል የተባበሩት መንግሥታት ከገዳሪፍ ወደ ከሰላ ሾክ በተብለ ቦታ ጽ. ቤት ያስከፈቱትን እንዳያዘጉቸው፣ ሁለተኛ በራስ መንገሻ የኢዴኅ ጦር የሰፈረው ደራብል (ከአምራኩባ አጠገብ) ሲሆን አንድ ቀን እንዳይወሪራቸው ነው። ሥጋታቸው ምን ያህል እዉነት እንደሆን  መልሱን ከተከብሩ ልዑል ራስ መንገሻ በትኅትና እንጠብቃለን።

# ክፍል ሰባት

## ባጎረስኩት እጄን ተነከስኩ

ንጉሥ ኃይለ የአፍሪካን አንድነት ለመሥረት ወይይት የጀመሩት ከኢትዮጵያ ጎረበት አገሮች እንደሆነ ይነገራል። በተለይ በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ የኢትዮጵያ አርበኞች ነጭ ሠራዊትን ማየት ስለማይፈልጉ በኢንግሊዝ ወታደሮች ላይ አደጋ እንዳያደርሱ ስለተፈራ ንጉሡ ወደ ሱዳን መጥተው አርበኛው ለኢንግሊዝ ወታደር እንዲታዘዝ መመርያ ከኢንግሊዝ መንግሥት ለመከላከያ ተላለፈ። ንጉሡ ከኢንግልዝ አገር እስከሚወጡ ድረስ እቅዳቸውን በአዎንታ ተቀበሉ፣ ንጉሡ ሱዳን እንደረሱ ከካርቱም ደቡብ ራቅ ወደለ ቦታ ጀበል አውልያ እንዲቆዩ ተነግሯቸው 150 የሱዳን ወታድሮች ጠባቂ መድቡላቸው፣ ከዚያም በየ 15 ቀን የሚጎበኛቸው ሰው መድበውላቸው ተከታይ ትዕዛዝ እንዲጠባበቁ መመሪያ ተሰጣቸው። ኃይለ ሥላሴ ብዙም ሳቆዩ ከአርበኞች ጋር በሚስጥር ተገናኝተው 150 የሱዳን ወታድርችን አስከትለው በጎጃም በኩል አሜድላ ገብተው ሰቀላ በምትባል መንደር ገብተው የኢትዮጵያን ባንደራ ሰቀሉ። እርሳቸው ሲደርሱ አርበኛው ድል እየተቀዳጀ ነበርና አርበኛው «ነጭ ሁሉ አንድ ነውና የኢትዮጵያን መሬት ወዮልህ ወደማለት የተቃረበውን አርበኛ በማረጋጋት ያለ ግጭት ሥራው ቀጠለ። ጎሬቤት አገር ሱዳንን በጣም አቀርቡ። ለችግር ቀን ወዳጅ ትሆናለች ብለው አሰቡ እንጂ በችግር ቀን ችግር ፈጣሪ ይሆናሉ ሳይገምቱ ብዙ ውሌታ ዋሉላቸው።

ኃይለ ሥላሴ ለሱዳን ውሌታ በቀላሉ የሚገመት አይድለም፣ ጉልህ ሆነው ከሚታዩት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉ ናቸው፤

1ኛ ሱዳን ከኢንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነፃ እንዲትወጣ በተ.ተ.መ. ስብሰባ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተከራከረዋል፣ የስዳኖችም ድምጽ እንድሰማ አድርገዋል።

2ኛ ለሱዳን ነፃነት መታደል ዋስ ሆነው የፈርሙ ጃንሆይ ነበሩ።(በዚህ ጽሑፌ ለሱዳን ነፃነት ታደለ ብዬ የጻፍኩት። ሱዳኖች ለነፃነት በአደባባይ ቆመው ሳይከራከሩ፣እጫካ ዘልቀው ሳይታኮሱ፣ ለአመፃ ሰላማዊ ሠልፍ ሳይወጡ፣ ቁርስ አቅርበው ሊበሉ ሲሉ ነፃነት ውሰዱ ተባሉና ታደሉ። ለዚህ መታደላቸውን የደጋገምኩት፡

3ኛ የሱዳን ወታደሮች ይለብሱት የነበርውን ጀለብያ ቀይርው ቁምጣና ሸሚዝ እንዲለብሱ ያደረጉ ኃይለ ሥላሰ ናቸው፣ በወቅቱ ቁምጣና ሸሚዙ መግዣም ከኢትዮጵያ በጀት እንደነበረ በርካታ ሱዳኖች ያነሳሉ፣ ስለቁምጣው አተውካኮስ የኢትዮጵያ ወታደሮች ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን ተልከው ለወራት እንዳስተምሯቸው የሱዳን የቀድሞ ወታደሮች በውሌታ መልከ ቢያነሱም ከፋታቸውን አይተውም።

4ኛ ሱዳን በአፄ ሃይለ ሥላሰ ትግል ነፃ ብትወጣም ስለውጭ እንግዳ አቀባበል ምንም ግንዛቤ አልነበራቸውም ይባላል፣ ስለሆነም የውጭ ልዑክ ሲመጣ ተመሳሳይ ማዕረግ ያለው ወደ የግል መኖሪያው ወስዶት ያስተናግደው ነበር፣ ለምሳሌ የአንድ አገር የሚኒስተር፣ ትምህርት ሚኒስተር ወደ ሱዳን ቢመጣ የሱዳን የትምህርት ሚኒሰተር ወደ ቤቱ ወስዶት ያስተናግደዋል ማለት ነው፣ መልዕክተኛው የመጣበትን አጠናቅቆ ወደ አገሩ ሲመለስ እስከ መሳፈሪያው ድረስ የሚያደርስው የትምህርት ሚኒስተሩ ነው፣ እንዲሁ ሁሉም የመጣውን እንግዳቸውን ይቀበላሉ፣ ይሸኟቸዋልም፣ ተሰብስበው እንግዳን የመቀበል ወይም የመሸኘት ልምድ አልነበራቸውም፣ ኃይለ ሥላሰ ሁኔትውን ተመልከተው ስለእንግዳ አቀባበልና አሸኛኘት አስተምረዋቸው በራሳቸው ገንዘብ *የአፍሪካ ሆቴል* የሚባል አሠርተው አስረከቧቸው፣ ይህ ሆቴል እስከ አሁን ድረስ እያገለገላቸው ነው፣

5ኛ የሱዳን ዋና ከተማ ካርቱም ተብሎ ቢጠራም የሦስት ከተሞች ቅንጅት ነው፣ አምዱሩማን፣ሰሜን ካርቱም ወይም ባሕሪ እና ካርቱም ራሱ ካርቱም ሲሆን ሦስቱም በአባይ ይለያያሉ፣ ከባሕሪ ወደ አምዱሩማን ለመሻገር አስቸጋሪ ስለነበረ ኃይለ ሥላሰ ድልድይ እንዲሠሩ መክረዋቸው ግማሹን ወጪ እንደረዷቸው ብዙ ሱዳኖች ይናገራሉ፣ የድልድዩ ርዝመት ከ300 ሜትር በላይ ነው፡

6ኛ ሱዳን ነፃነት ስታደላት ደቡብ ሱዳን በፌዴሬሽን እንድትተዳደር የፀደቀ ውል ነበር፣ ስግብግቧ ሰሜን ሱዳን ግን ውሉን ጨፍልቃ በክርስቲያኑ ደቡብ ሱዳን ጦርነት አወጀች፣ ኃይለ ሥላሰ ጣልቃ ገብነት በ1972 ዓም እርቅ ተደረገና *ኛኛቱ 2 ውል በሁለቱም ወግኖች ተፈረመ።*

ኛኛቱ የሚለው በጭብጥ መተርጎም ቢከብደኝም ሐሳቡ በግርድፉ የጋራ ስምምነት መሆኑን አንድ የደቡብ ሱዳን ተወላጅ ነግሮኛል፡እዚህ ላይ ስለትርጉሙ ባያስጨንቅም ጽንሰ ሓሳቡ ያን ጊዜ ገዳሪፍ ከሰላ የኢትዮጵያ ስለነበሩ *«ከሰላ ወደ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ እንዲቀለሉ የሚል* ነበር። ውሉ እስከ አሁን በደቡብ ሱዳን አልተጣሰም፣ ኃይለ ሥላሰ ጉዳዩ ትኩረት ሰጠተው ብንቀሳቀሱም በውስጥ ችግር ምክንያት ውህደቱን ሊፈጽሙ ሣይችሉ ተገለበጡ፥ በለስ ያደለው አራዳው የሱዳን አስተዳደር ከሰላን ላጥ አድርጎ ግዛቴ ነው ብሎ ቁጭ አለ። ኃይለ ሥላሰ የጀመሩትን ከግብ የሚያደርስ አመራር በኢትዮጵያ በመታጣቱ ሱዳን ዛሬ እየፎለለብን ነው። የዛሬ መሪዎቻችን ከሱዳን አብረው ሕዝባችንን በማሳደድ፣ የኢትዮጵያንም መሬት ገምሰው ለሌላ አገር መስጠት እንጂ ወሰን ሲያቀኑ አይታዩም። ስለአራት ኪሎ ቤተመንግሥት እንጂ ስለአገርም ሆነ ስለሚመሩት ዜጎች ደንታ ያላቸው አይምስሉም።

ደቡብ ሱዳኖች በቃላቸው ፀንተው መጪውን ጊዜ እይተጠባበቁ ናቸው። ብዙዎቹ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት ሲመሠረት የኛኛቱ 2 ስምምነት ተፍፃሚ ይሆናል የሚል ተስፋ እንዳላቸው በግልጽ ሲናገሩ ይሰማል።

# *ክፍል ስምንት*

## *ከኒመሪ ወዳጅነት የዚያድ ባረ ጠላትነት*

ኃይለ ሥላሰ ይህን ሁሉ በጎ ሥራ ሲሠሩላቸው ሱዳኖች ግን የመቀበሪያ ጉድጓድ ሲቆፍሩላቸው ነበር። ኢትዮጵያን ለማፍረስ ያቀዱት አገር ተብለው ሣይታሰቡ ነው። ሱዳኖች አይነቃብንም ብለው ሤራ ቢሠሩም ከንገሱ የሚመልጥ መረጃ ስላልነበረ አዘውትረው *«ከኒመሪ ወዳጅነት የዚያድ ባረ ጠላትነት ይሻለኛል» ይሉ ነበር።*

የሱዳን ምኞት ኢትዮጵያን ለመደምሰስ ነው፣ ኢትዮጵያ እስካልጠፋች ምንም እረፍት የላትም፣ ሱዳኖች መሪዎቻችን በአፍ እየአሸነገሏቸው በሚስጥር መሬታችንን እየዘረፉ ናቸው። መለስ ከሱዳን ተመርቆ አራት ኪሎ በቴመንግሥት እንደገባ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የሱዳን ሰኩሪቲዎች ኢትዮጵያን አጥለቀለቋት፡ የንጉሣችን መኝታ ቤት፣ ሽንት ቤት ሣይቀር በካሜራና በቪዲዮ ቀርፀው እንዲሁም በጅ ስዕል እየሳሉ ሲወስዱ የወያኔ ጸጥታም ይተባበራቸው ነበር። የሱዳን ፀጥታ የአገራችንን ቅርስ ዘርፈዋል። ከተዘረፉ ዶኩሜንቶችም መካከል ጠቃሚ ቅርሶች ለመላ አረብ አገሮች ተበትነዋል፤ ከላይ ለመግልጽ እንደሞኮርኩት መለስ ሱዳኖች ተቃዋሚን እስካላስተናገዱ ከትግራይ መሬት ውጪ የፈለጉትን መውሰድ እንደሚችሉ ቃል ስለገባላቸው የልብ ልብ ተሰምቷቸው የአባይ ወንዝ የሚሄድበት የኛ ነው እያሉ ነው። ኢትዮጵያን ለጥቃት ሊያጋልጡ የተነሱ መሪዎቻችን እንጂ ጠላትማ ጉንደት ጉዳጉዲ፣ ጉራ ላይ፣ አድዋ ላይ፣ ሰሃጢ፣ዶግሌ፣ደራብል(መተማ) እጁን ተከርክ እግሩን ተሰናክሎ አርፎ ተቀምጧል።

ኢትዮጵያ ከማንም ጎረቤት አገር ጋር የድንበር ክልል የላትም እየተባለች ትታማለች። ይህ አባባል ለብዙ ሰዎች አወዛጋቢ መስሎ ነው የሚታያቸው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ የብዙ ሺዎች የነፃነት ታሪክ ያላት አገር ሆና ሳለች እንዴት ነው ካልነበሩት አገሮች ጋር ድንበር የምትካለለው?? ከላይ

ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ሱዳን የምትባል አገር የትኛዋ ናት? ሣህል አገሮች «እኛም ሁላችን ጥቁሮች ስለሆንን መሬት እንካፈል ቢሉ ለሱዳን እንደሚሰጠው ሰንትራል አፍሪካ ወይም ቻድ መሬት ከኢትዮጵያ ይሰጠን ብለው ክርክር ቢያነሱ የሚከለክላቸው የሕግ አንቀጽ አለ ወይ? የለም። ስለሆነም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ስለሆነ ቢታሰብበት ይበጃል።

ክፍል ዘጠኝ

ይ ቀ ጥ ላ ል.........

አዘጋጅ »«አባተ ደጋጎ»